የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግሥት
የሰብአዊ አገልግሎቶች (DEPARTMENT OF HUMAN SERVICES)

# SNAP/CASH የዳግም-ማረጋገጫ ቅጽ

**የእርስዎ ተጨማሪ የምግብ እርዳታ ፕሮግራም (ሳፕሊመንታል ኑትሪሽን አሲስታንስ ፕሮግራም) (SNAP) እና/ወይም የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ (ካሽ አሲስታንስ) ጥቅማጥቅሞች ይህን ቅጽ የማይመልሱ ከሆነ ያበቃሉ!**

የተጠየቀውን መረጃ በዚህ ቅፅ የሚንፈልገው እርስዎ አሁንም ብቁ መሆንዎን ለማየት እና ወርሃዊ የSNAP እና/ወይም የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ጥቅማጥቅሞችዎን መጠን ለማስላት ነው። እኛ በተያያዘው ቅጽ ውስጥ ስለጠየቅናቸው፣ ለመጨረሻ ጊዜ ማመልከቻ ወይም ዳግም-ማረጋገጫ ካጠናቀቁ በኋላ የተከሰቱ፣ ማንኛውም ለውጦችን ሪፖርት ማድረግ አለብዎት።

ለጥያቄዎቹ መልስ በሚሰጡብት ጊዜ፣ በጥቅማጥቅም ቤተሰብዎ ውስጥ ስለተካተቱት እያንዳንዱ ሰው መረጃ መስጠት አለብዎት። ይህ ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ ነገር ግን በስደተኝነት ሁኔታቸው ምክንያት የእርስዎ ጉዳይ ውስጥ ያልተካተቱ ወላጆች ወይም የትዳር አጋሮችን ያካትታል። ይህም ስፖንሰሩ ቤትዎ ውስጥ የማይኖር ቢሆንም እንኳን፣ ዜጋ ያልሆነ ሰውን ስፖንሰር የሚያደርግ ሰው መረጃን ያካትታል።

ከመልስዎ የትኛዉንም ለማብራራት ወይም ተጨማሪ መረጃን ለመስጠት የብቻ ወረቀት ሊጠቀሙ ይችላሉ። የትኛዉም የብቻ ወረቀት ከዚህ ቅፅ ጋር መላክ አለበት።

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምርያ (DHS) አገልግሎት ማዕከል ሳይጎብኙ ይህንን ቅጽ መሙላት እና ከሚቀጥሉት በአንዱ የማረጋገጫ ሰነዶችን ማቅረብ ይችላሉ፥

- **ደብዳቤ፣** የተያያዘውን ቅጽ ሞልተው ይፈርሙ እና ለውጦችዎን ለማረጋገጥ የሚጠቅሙ ከማንኛውም የማስረጃ ቅጂዎች ጋር በፖስታ ይላኩልን፣ ወደ፥

  የዲሲ ሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ
  የጉዳይ መዝገብ መቆጣጠሪያ ክፍል
  P.O. Box 91560
  Washington, DC 20090

- **ፋክስ፥** የኢኮኖሚያዊ ዋስትና አስተዳደር (Economic Security Administration (ESA)) (202) 671-4400

በተጨማሪም፣ ቅጹን ሞልተው መፈረም እና ለውጦችዎን ለማረጋገጥ የሚጠቅሙ ከማንኛውም የማስረጃ ቅጂዎች ጋር ከሶስቱ ክፍት የአገልግሎት ማዕከላችን ወደ አንዱ መዉሰድ ይችሉ ይሆናል፥

*Anacostia* 2100 Martin Luther King Jr. Avenue, SE
*Congress Heights (ኮንግረስ ሄይትስ) የአገልግሎት ማእከል* 4049 South Capitol (ሳውዝ ካፒቶል) መንገድ፣ SW
*H የመንገድ አገልግሎት ማእከል* 645 H Street NE

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግሥት
የሰብአዊ አገልግሎቶች (DEPARTMENT OF HUMAN SERVICES)

**SNAP/CASH የዳግም-ማረጋገጫ ቅጽ**

**ይህንን ቅጽ ለመሙላት ዕርዳታ ከፈለጉ በዚህ ቁጥር ይደዉሉ፥ (202) 727-5355 TTY/TDD፥ 711 (855) 532-5465።**

**የእርስዎ መረጃ**

| ሙሉ ስም፣ | የትውልድ ቀን (ወወ/ቀቀ/ዓዓዓዓ)፥ | የስልክ ቁጥር፣ | የእርስዎ የጉዳይ ቁጥር (የሚታወቅ ከሆነ)፥ |
|---|---|---|---|
| | | | |

**ጥያቄ #1፥ የተገኘ ገቢ ለዉጦች**

| | |
|---|---|
| ከመጨረሻው ማመልከቻዎ/ዳግም-ማረጋገጫዎ ቀን በኋላ፣ ሥራዎችን በመጀመሩ፣ በማቆሙ፣ ወይም በመቀየሩ ምክንያት የማንም ሰዉ ገቢ በ$100 በወር በላይ ተለዉጧል? | ❑ አዎ ❑ አይ |
| ከመጨረሻው ማመልከቻዎ/ዳግም-ማረጋገጫዎ ቀን በኋላ፣ የእርስዎ ቤተሰብ ያገኝ የነበረ መጠን ዉስጥ በወር $100 በላይ ለዉጥ ነበረው? | ❑ አዎ ❑ አይ |

*ለየትኛዉም ከላይ ያሉ ጥያቄዎች መልስዎ አዎ ከሆነ፣ ካለፉት 30 ቀናት የደሞዝዎን መጠን ከታች ያሉ ሳጥኖች ዉስጥ ያስገቡ እና ማስረጃዉን ያያይዙ።*

| ማን | አሰሪ | የጀመሩበት ቀን (ሥራ ጀምረው ወይም ቀይረው ከሆነ) | ያቆሙበት ቀን (ሥራ አቁመው ከሆነ) | የክፍያ ቀን | መጠን | የክፍያ ቀን | መጠን | የክፍያ ቀን | መጠን | የክፍያ ቀን | መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | $ | | $ | | $ | | $ |
| | | | | | $ | | $ | | $ | | $ |

**ጥያቄ #2፥ ያልተጣራ ገቢ ለዉጦች**

ከመጨረሻው ማመልከቻዎ/ዳግም-ማረጋገጫዎ ቀን በኋላ፣ በየትኛዉም ዓይነት ያልተጣራ/ያልተገኘ ገቢ ዉስጥ ቤተሰብዎ የ$100 በላይ ለዉጥ ነበረዉ? ❑ አዎ ❑ አይ

***ያልተጣራ/ያልተገኘ ገቢ ዓይነቶች*** *የሚያካትቱት SSI፣ የአረጋዉያን ጥቅማጥቅሞች፣ የሥራ ማጣት ክፍያ፣ የማሳደጊያ እንክብካቤ/ጉድፈቻ ድጎማ፣ የፍቺ ካሳ ክፍያ፣ ወዘተ*

መልስዎ አዎ ከሆነ፣ ከታች ያለዉን ሳጥን ይሙሉ እና ማስረጃን ያያይዙ።

| ማን | መጠን | ቀን | ምን ያህል ደጋግመዉ ወሰዱ? | አይነት |
|---|---|---|---|---|
| | $ | | | |
| | $ | | | |

### ጥያቄ #3፥ የቤተሰብ አባል ለዉጦች

ከመጨረሻው የማመልከቻ/የዳግም-ማረጋገጫዎ ቀን በኋላ፣ የቤተሰብዎ አባልነት ላይ ማንኛውም ለውጦች ነበሩ?
*ይህ የገቡ ወይም የወጡ ሰዎችን፣ ልደቶችን፣ ሞቶችን፣ ወዘተ ሊያካትት ይችላል።*

❑ አዎ ❑ አይ
አዎ ከሆነ፣ ከዚህ በታች ያለዉን ክፍል ይሙሉ

| የአያት ስም | የመጀመሪያ ስም | የአባት ስም | የትውልድ ቀን | የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር | ከእርስዎ ጋር ያለው ግንኙነት (ልጅ፣ አክስት፣ ወዘተ) | ባንድ ላይ ትበላላቹ? | U.S. ዜጋ? | የገቡት ወይም የወጡት መቼ ነዉ? |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ❑አዎ ❑አይ | ❑አዎ ❑አይ | ወር፥ አመት፣ |
| | | | | | | ❑አዎ ❑አይ | ❑አዎ ❑አይ | ወር፥ አመት፣ |
| | | | | | | ❑አዎ ❑አይ | ❑አዎ ❑አይ | ወር፥ አመት፣ |

### ጥያቄ #4፥ የልጅ ድጋፍ ክፍያ ለዉጦች

ከመጨረሻው የማመልከቻ/የዳግም-ማረጋገጫዎ ቀን በኋላ፣ ቤተሰብ ዉስጥ ለማይኖር ሰዉ በፍርድ ቤት የታዘዘ የልጅ ድጋፍ ለመክፈል የህግ ግዴታ ላይ ለዉጥ የነበረው ማንም ሰዉ አለ?

❑ አዎ ❑ አይ
መልስዎ አዎ ከሆነ፣ ከታች ያለዉን ክፍል ይሙሉ <u>እና</u> ማስረጃን ያያይዙ።

| ማን ነዉ የከፈለዉ? | ለየትኛዉ ልጅ? | ህጋዊ ግዴታ ወርሃዊ መጠን | ወርሃዊ መጠን በትክክል የተከፈለው |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |

### ጥያቄ #5፥ የአድራሻ እና የመጠለያ ወጪ ለዉጦች

ከመጨረሻው የማመልከቻ/የዳግም-ማረጋገጫዎ ቀን በኋላ፣ የመጠለያ ወጪዎ ላይ ለውጥ ያስከተለ ቤት ቀይረዋል ወይም የአድራሻ ለውጥ አድርገዋል?

❑ አዎ ❑ አይ
አዎ ከሆነ፣ ይህንን ክፍል ይሙሉ <u>እና</u> ኪራይ፣ ግብር፣ መገልገያዎች የመሳሰሉ የአሁኑ የመጠለያ ክፍያዎችዎን ማረጋገጫ ያያይዙ

**አዲሱ አድራሻ፥** ________________________ ________ ________ ______ ______
ሰፈር አፓት # ከተማ ኢስቴት ዚፕ

| | |
|---|---|
| አሁን ኪራይ ወይም ብድር ክፍያ በወር፥<br>**$** | አሁን **የንብረት ግብር** በወር፥<br>**$** |
| አሁን **የቤት ባለቤቶች መድን** በወር፥<br>**$** | አሁን **የኮንዶ ክፍያዎች/ HOAዎች** በወር፥<br>**$** |

አሁን ተጠያቂ የሚሆኑላቸው ሁሉንም ያጣሩ፥

❑ መብራት ❑ ጋዝ ❑ ነዳጅ ❑ ዉሃ ❑ ስልክ (ሞባይል ጨምሮ) ❑ ሌላ፥

**ጥያቄ #6**

ቤተሰብዎ ዕድሜያቸው ከ60 በላይ የሆነ አባል እና/ወይም አካል ጉዳተኛ የሆነ አባል የሚያካትት ከሆነ፣ ቀጥሎ ያለዉን ጥያቄ ይመልሱ፥

ከመጨረሻው የማመልከቻ/የዳግም-ማረጋገጫዎ ቀን በኋላ፣ እንደ ጥሬ ገንዘብ፣ የባንክ ሂሳቦች፣ አክሲዮኖች፣ ቦንዶች፣ በየጊዜው የሚከፈሉ የጡረታ አበሎች፣ *ወዘተ.* የመሳሰሉ ሀብቶች ላይ ለውጥ የነበረው ማንኛውም ሰው አለ? ❑ አዎ ❑ አይ

*መልስዎ አዎ ከሆነ፣ ማስረጃን ያያይዙ።*

**ጥያቄ #7 – ለጊዜያዊ እርዳታ ለችግረኛ ቤተሰቦች (Temporary Assistance for Needy Families)(TANF)/የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ (ካሽ አሲስታንስ) ደንበኞች ብቻ**

በጉዳዮ ውስጥ ካሉት ማንኛውም ልጅ ከቤት ውጪ የሚኖር ወላጅ አለው? ❑ አዎ ❑ አይ

*አዎ ከሆነ፣ ከታች ይሙሉ።*

ለተወሰነ የጥሬ ገንዘብ እርዳታ እንደ ብቁነት መስፈርት፣ ጥቅማጥቅሞችን ከሚጠይቁላቸው ልጆች ማናቸውም ከቤት የቀረ/አብሮ የማይኖር ወላጅ ያለው ካለ፣ ለDHS መናገር አለብዎት። ለቀሪው ወላጅ ዝርዝሮችን ማቅረብ የማይፈልጉ ለሆነ፣ እባክዎ ይህን መረጃ ከማቅረብ እንዲታለፉ የሚፈቅዱልዎ ምክንያቶች ዝርዝርን ለማግኘት፣ ከዚህ ቅጽ ጋር የተያያዘውን የTANF ስምምነት ይመልከቱ።

❑ አሳዳጊ-ያልሆነ ወላጅ በተመለከተ መረጃ ከማቅረብ ሊታለፉ እንደሚችሉ ካሰቡ፣ እዚህ ይጫኑ

❑ እኔ ከራሴ ከDHS ወይም የህጻን ድጋፍ ሰራተኛ ጋር መወያየትን እመርጣለሁ።

ጥያቄ 7ን (ይህ ጥያቄ) እንዳነበብኩ እና በጥያቄው ውስጥ ስለወላጅነት እና አባትነት የተጻፉት ፍሬ ነገሮች በኔ የግል እውቀት፣ መረጃ እና እምነት መሰረት እውነት መሆናቸውን፣ በሀሰተኛ ምስክርነት የወንጀል ቅጣቶች ስር በእውነት እምላለሁ ወይም አረጋግጣለሁ። እኔ የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ (ካሽ አሲስታንስ) ከተቀበልኩ፣ ሁሉም የልጅ እርዳታ ክፍያዎች ኮሎምቢያ ዲስትሪክት፣ የጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ የልጅ እርዳታ አገልግሎቶች ክፍል (Child Support Services Division, CSSD) እንደሚሰበሰብ እና እንደሚሰራጭ እረዳለሁ እና እስማማለሁ። እኔ የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ (ካሽ አሲስታንስ) እየተቀበልኩ ለመደገፍ ያለኝን መብቶች እየመደብኩ መሆኑን እረዳለሁ። እኔ ከእነዚህ ፕሮግራሞች የሚቀበለው መጠን ያህል ለድጋፍ እመድባለሁ። የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ (ካሽ አሲስታንስ) እያገኘሁ ከሆነ፣ የጥሬ ገንዘብ እርዳታ ስጦታን የሚበልጥ ተጨማሪ የልጅ ድጋፍ ክፍያዎችን ሊያገኝ እችላለሁ። በስህተት ክፍያ ከተቀበልኩ፣ ከዚያ CSSDን አገኛለሁ። ማንኛውም በስህተት የተገኙ ክፍያዎች ለCSSD መመለስ እንዳለባቸው እና ለCSSD መልሼ ለመክፈል እንደምገደድ እረዳለሁ። የልጅ እርዳታ የማልፈልግበት ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ እረዳለሁ፣ ነገር ግን ከCSSD ጋር መተባበር አስፈላጊ መሆኑን እረዳለሁ። ስለዚህ፣ ምንም አይነት ስጋቶች ካሉኝ የCSSD የጉዳይ ሰራተኛን ወዲያዉኑ አገኛለሁ።

እዚህ ይፈርሙ፥ ______________________________ ቀን፥ ______________

*ደንበኛ ወይም ስልጣን ያለው ተወካይ ፊርማ*

ቀሪ ወላጅ(ጆች) ላይ የቀረበ **ከታች** ያለውን መረጃ ይሙሉ፣ **ለልጅ የጥሬ ገንዘብ እርዳታ ዳግም-እያረጋገጡ ከሆነ ብቻ።**

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግሥት
የሰብአዊ አገልግሎቶች (DEPARTMENT OF HUMAN SERVICES)

**SNAP/CASH የዳግም-ማረጋገጫ ቅጽ**

| ልጅ አንድ | | | |
|---|---|---|---|
| የልጁ ሙሉ ስም፣ | | **የልጅ የትውልድ ቀን፥** | |
| ልጁ/ጅቷ የተጸነሰበት/ችበት ከተማ እና ስቴት፥ | | | |
| *አሳዳጊ-ያልሆነ/ቀሪ ስለተባለው ወላጅ ይንገሩን (ያለዎትን ሁሉንም መረጃ ይስጡ)፥* | | | |
| የወላጅ ሙሉ ስም፥ | | ቅጽል ስም (ካለ)፥ | |
| የትውልድ ቀን፣ | የትውልድ ስፍራ፣ (ከተማ፣ ስቴት)፥ | | SSN፣ |
| ዘር፣ | | ስልክ ቁጥር፥ | |
| የመጨረሻ የሚታወቅ አሰሪ፣ | | የቅጥር ጊዜያት፣ | |
| አባትነት ተረጋግጧል? ❑ አዎ ❑ አይ | | | |
| የልጅ ቀለብ ችሎት/ግዛት፣ | | ከተማ፣ | አገር፣ |
| የታዘዘበት ቀን፣ | የታዘዘው መጠን፣ | አሳዳጊ-ካልሆነ ወላጅ ለመጨረሻ ጊዜ ገንዘብ የተቀበሉበት ቀን፥ | |

| ልጅ ሁለት | | | |
|---|---|---|---|
| የልጁ ሙሉ ስም፣ | | **የልጅ የትውልድ ቀን፥** | |
| ልጁ/ጅቷ የተጸነሰበት/ችበት ከተማ እና ስቴት፥ | | | |
| *አሳዳጊ-ያልሆነ/ቀሪ ስለተባለው ወላጅ ይንገሩን (ያሎትን ሁሉንም መረጃ ይስጡ)፥* | | | |
| የወላጅ ሙሉ ስም፥ | | ቅጽል ስም (ካለ)፥ | |
| የትውልድ ቀን፣ | የትውልድ ስፍራ፣ (ከተማ፣ ስቴት)፥ | | SSN፣ |
| ዘር፣ | | ስልክ ቁጥር፥ | |
| የመጨረሻ የሚታወቅ አሰሪ፣ | | የቅጥር ጊዜያት፣ | |
| አባትነት ተረጋግጧል? ❑ አዎ ❑ አይ | | | |
| የልጅ ቀለብ ችሎት/ግዛት፣ | | ከተማ፣ | አገር፣ |
| የታዘዘበት ቀን፣ | የታዘዘው መጠን፣ | አሳዳጊ-ካልሆነ ወላጅ ለመጨረሻ ጊዜ ገንዘብ የተቀበሉበት ቀን፥ | |

**አሳዳጊ-ያልሆኑ/ቀሪ ወላጆች የሌላቸው ከ2 በላይ ልጆች ካለዎት፣ እባክዎ የነሱን መረጃ በተጨማሪ ወረቀት ላይ ይዘርዝሩ።**

**SNAP/CASH የዳግም-ማረጋገጫ ቅጽ**

**ማረጋገጫ (የSNAP እና የጥሬ ገንዘብ እርዳታ)፥**

ይህ ቅፅ ላይ ያሉ ሁሉም መረጃዎቹ ትክክል እንደሆኑ አምናለሁ። ይህ ቅፅ ላይ ያሉ ሁሉም ለዉጦቼን ሪፖርት አድርጌያለሁ። የትኛዉንም ዉሸት መረጃ ከሰጠሁ፣ ህግ እየሰበርኩ ሊሆን እንደሚችል አዉቃለሁ። ይህ ቅፅ ላይ ሪፖርት ስላደረኳቸዉ ለዉጦች ምክንያት እርሱን አዉቃለሁ፣ ይሄም፥

1. *የእኔ SNAP (የምግብ ማህተሞች)እና/ወይም የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞች ሊቀንሱ ይችላሉ፤ ወይም*
2. *የእኔ SNAP (የምግብ ማህተሞች)እና/ወይም የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞች ሊቆሙ ይችላሉ።*

ከታች በመፈረም፣ እኔ DHS ስለኔ መረጃ እንዲያገኝ ፍቃዴን እሰጣለሁ። ይህንን DHS ከአሰሪየ፣ የቤት አከራየ፣ ባክን፣ እና የአገልግሎት ካምፓኒ ሊያገኝ ይችላል። እኔ ለDHS መረጃ እንዲሰጡ ለእነዚህ ሁሉም ሰዎች ፍቃዴን ሰጥቻለሁ። እኔ በዚህ ቅጽ ላይ ያለውን መረጃ ገምግሜያለሁ እና በዚህ መላው ቅጽ ላይ ያለው ሁሉም መረጃዬ እውነት እና ትክክል እንደሆነ አምናለሁ፣ በቤተሰቤ ውስጥ ያለው የእያንዳንዱ ሰው የዜግነት እና የውጭ ሀገር ዜግነት ሁኔታን የሚመለከት መረጃን ጨምሮ። እኔ ማንኛውንም ሀሰተኛ መረጃ ከሰጠሁ፣ ህጉን እየጣስኩ ሊሆን እንደሚችል እና የወንጀል ክስ እና ቅጣት ሊከተለኝ እንደሚችል አውቃለሁ። ይህንን መረጃ የክልል እና የፌደራል ባለስልጣናቶች እንደሚያረጋግጡት አውቃለሁ። እኔ በምርመራዎቻቸው ላይ ለመርዳት እስማማለሁ።

ፊርማ፥ X ______________________________ ቀን፣ ___/___/_____ የስራ ጊዜ ስልክ ቁጥር፣ (      )

ሕጋዊ ተወካይ ፊርማ X ______________________________ቀን፣ ___/___/_____ የስራ ጊዜ ስልክ ቁጥር፣ (      )

እርስዎ ለ **TANF** ዳግም-እያረጋገጡ ከሆነ፣ ከታች ያለውን መረጃ በ **TANF** **ብቻ** ስር ማንበብ እና መፈረም አለብዎት

**TANF ብቻ**

## የTANF ስምምነት (የጥሬ ገንዘብ ደንበኞች ብቻ)

**ለTANF ዳግም-እያረጋገጡ ከሆነ፣ ያንብቡ እና ይፈርሙ**

***የTANF የልጅ ድጋፍ ትብብር***

እርስዎ በቂ ምክንያት ከሌለዎ በሥተቀር፣ ለእርዳታ ብቁ ለመሆን አባትነትን ለማረጋገጥ እና የገንዘብ እና የህክምና ድጋፍ ለማግኘት ትብብር እንዲያደርጉ በህግ ይጠየቃሉ። በማናቸውም ጊዜ “በቂ ምክንያት” የሚለውን ክርክር ማቅረብ ይችላሉ። “በቂ ምክንያት” ያሎት ስለመሆኑ ደጋፊ ማስረጃ እስካቀረቡ ድረስ የልጅ ድጋፍ እና የአባትነት ማረጋገጫ ትብብር መስፈርት ቀሪ ሊደረግሎት ይችላል፣ ይህም ሊረጋገጥ የሚገባው በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ቢሮ የልጅ (Office of the Attorney General, OAG) ድጋፍ አገልግሎት ክፍል ( Child Support Services Division, CSSD) ጋር ስብሰባ ካደረጉ በኋላ ነው። አባትነት እና የልጅ ድጋፍ ማረጋገጥ ላይ ትብብር አለማድረግ ከTANF ገንዘብ ላይ 25% መቀጮ ሊያስከትል ይችላል። መተባበር ደግሞ ለልጅዎ የገንዘብ ሽልማት ወይም የህክምና ድጋፍ የማስገኘት አቅም አለው እና በቂ ምክንያት መኖሩ ሳይወሰን አለመተባበር ግን የTANF የገንዘብ ድጋፍዎ ላይ ቅጣት ሊያስከትል ይችላል። CSSD በቂ ምክንያት መኖሩን የሚደግፍ ማስረጃ ማግኘት ላይ ተገቢ የሆነ እርዳታ ያደርጋል።

በቂ ምክንያት መኖሩን ከሚያሳዩት ውስጥ፣ ለመተባበር የሚደረገው ጥረቶች ድጋፍ በሚጠየቅለት ልጅ ላይ፣ በአመልካቹ ወይም ተቀባዩ ላይ፣ በአመልካቹ ወይም ተቀባይ የቤተሰብ አባል ላይ፣ ወይም በአመልካቹ ወይም ተቀባይ የቅርብ ዘመድ ላይ አካላዊ፣ወሲባዊ ወይም ስሜታዊ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ምክንያታዊ ግምት ካለ ፣ ወይም ድጋፍ የተጠየቀለት ልጅን በተመለከተ የሚደረጉ ትብብሮች ወይም ከትብብሮቹ የተገኙ ውጤቶች ለልጁ ጎጂ መሆኑን CSSD የለያቸው ሁኔታዎ ካሉ፣ ነገር ግን ከሚከተሉት ባንዱ (1) ያልተወሰነ፥

1. ልጁ የተጸነሰው በዘመዳሞች መካከል በሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት ወይም በጾታዊ ጥቃት ምክንያት ነው (ይህ ንኡስ አንቀጽ ተፈጻሚ እንዲሆን በዘመዳሞች መካከል በሚደረግ የግብረስጋ ግንኙነት ምክንያት ወይም በጾታዊ ጥቃት ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ መኖር አስፈላጊ አይደለም)፤
2. ስልጣን ባለው ፍርድቤት የልጁ የጉዲፈቻ ክርክር በቀጠሮ ላይ ነው፤ ወይም
3. አመልካቹ ወይም ተቀባዩ ልጁን ለማሳደግ ወይም ለጉዲፈቻ መስጠትን የሚለውን ለመፍታት በህዝብ ወይም ፍቃድ ባለው የግል የማህበራዊ ኤጄንሲ ባሁኑ ጊዜ  እርዳታ እያገኘ ነው።

በቀረበው ደጋፊ ማስረጃ እና ማንኛውም አስፈላጊ ምርመራ መሰረት፣ CSSD ድጋፍ የተጠየቀበትን ልጅ አስመልክቶ ትብብር ማድረግ ለልጁ ፍላጎት ተመራጭ ስለመሆኑ ይወስናል፣ ለውሳኔው ምክንያቶችን ይለያል ፣እና ለአመልካች ወይም ተቀባይ ውሳኔውን እና ምክንያቶቹን በጽሁፍ ይሰጣል። መብቶቹ የሚያካትቱት፣ CSSD አመልካቹ ወይም ተቀባዩ ላለመተባበር በቂ ምክንያት እንደሌለው ከወሰነ እና አመልካቹ ወይም ተቀባዩ ላለመተባበር ከመረጠ ባለመተባበር ምክንያት የሚጣልበትን ቅጣት አስመልክቶ ፍትሀዊ በይግባኝ የመሰማት መብት። በCSSD ያሉ ባለሞያዎች የሰራተኞቹን ግኝቶች፣ እንዲሁም የበቂ ምክንያት ውሳኔ ለማስጠት የቀረቡ ምክንያቶችን ይመረምራል፣ እና ላለመተባበር በቂ ምክንያት ስለመኖሩ በሚደረጉ ክርክሮች ላይ ሊሳተፍ ይችላል። በCSSD ያሉ ባለሞያዎች፣ የበቂ ምክንያት ክርክር በቀጠሮ ላይ እያለ ወይም ይህ ከተረጋገጠ፣ አባትነትን ለማረጋገጥ፣ ድጋፍ ለማሰባሰብ፣የሶስተኛ ወገን ማስረጃ መሰብሰብ፣ ወይም ለህክምና ጉዳቶች ሃላፊ የሆኑ ሰዎችን መከታተል መሞከር የለባቸውም። CSSD እና ESA የእርስዎ እና የልጅዎ አድራሻ በሚስጥር መጠበቁን ማረጋገጥ እና ለመጠበቅ ማናቸውም እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፣ የሚከተሉት ከሆኑ፥ የበቂ ምክንያት መኖሩን በተመለከተ ክርክሩ በቀጠሮ ላይ ነው ወይም ተሰጥቷል፤ እርስዎን እና ልጅዎን በተመለከተ ሲቪል ወይም ጊዜያዊ የጥበቃ ትእዛዝ ከተሰጠ፤ ወይም CSSD የመረጃው መውጣት ለእርስዎ ወይም ለልጅዎ ጉዳት እንደሚያመጣ ምክንያት ካለው፤ እና አመልካቹ ወይም ተቀባዩ በቂ ምክንያት መኖሩን ለማስረዳት ተገቢ ጥረት እያደረጉ ከሆነ፣ የበቂ ምክንያት ክርክሩ ውጤት ሳይታወቅ የTANF ጥቅማጥቅሞች ሊከለከሉ፣ ሊዘገዩ፣ ሊቀሩ ወይም ሊቋረጡ አይችሉም።

***የTANF የቤት ውስጥ መኖር መስፈርትን አለማሟላት - እርጉዝ ወይም ልጅ አሳዳጊ/ ወላጅ ወጣቶች***

ወጣት ነፍሰጡር ወይም እናት እንደመሆንዎ በቤት ውስጥ መኖር መስፈርቶቹን በተመለከተ የብቃት መስፈርቶችን፣ መብቶችን፣ እና ሃላፊነቶችን እና ቀሪ የመሆን መብቶችን ማሟላት አለብዎት። ወጣት ነፍሰጡር ወይም እናት የሆነች የTANF ጥቅማጥቅሞች አመልካች ወይም ተቀባይ እና አግቢታ የማታውቅ ለTANF ጥቅማጥቅሞች ብቁ የምትሆነው ወጣቷ እና የወጣቷ ልጅ የሚኖሩት በወጣቷ ነፍሰጡር ወይም እናት ወላጅ ወይም ህጋዊ ሞግዚት መኖሪያ ውስጥ የምትኖር ወይም በከንቲባው በሚወሰነው መሰረት በሌላ የወጣት ነፍሰጡር ወይም እናት አዋቂ ዘመድ፣ ወላጅ፣ ሞግዚት፣ ወይም አዋቂ ዘመድ፣ ከዚህ በስተቀር፣

1. ወጣት ነፍሰጡሯ ወይም እናት በህይወት ያለ ወላጅ፣ ህጋዊ ሞግዚት፣ ወይም ሌላ ተገቢ አዋቂ ዘመድ የላትም፣
    a. የወጣቷ ነፍሰጡር ወይም እናት ህጋዊ ሞግዚት ለመሆን ብቃት ሊኖረው የሚችለው ወላጅ፣ ህጋዊ ሞግዚት፣ ወይም ሌላ ተገቢ አዋቂ ዘመድ ወጣቷ ነፍሰጡር ወይም እናት በሱ ወይም በሷ መኖሪያ ቤት ውስጥ እንድትኖር አልፈቀዱም።
    b. መምሪያው፣ በከንቲባው በወጡ ደምቦች መሰረት ከሚደረገው ምርመራ በኋላ፣ ከወጣቷ ነፍሰጡር ወይም እናት ወላጅ፣ ሞግዚት ወይም ሌላ አዋቂ ዘመድ ጋር አብረው ቢኖሩ፣ የአመልካች፣ ተቀባይ፣ ወይም ጥገኛ ልጅ የአካል ወይም የስሜት ጤንነት ወይም ደህንነት አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል ከወሰነ፣ ወይም
    c. መምሪያው፣ በከንቲባው በወጡ ደምቦች መሰረት፣ ሁኔታዎች ለአመልካች ወይም ተቀባይ በቂ ምክንያት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጡ መሆኑን እና ጥገኛው ልጅ ከወጣቷ ነፍሰጡር ወይም እናት ወላጅ፣ ሞግዚት፣ ወይም ሌላ አዋቂ ዘመድ ውጭ በሚኖሩበት ጊዜ እርዳታ ማግኘታቸው የበቂ ምክንያት ውሳኔ እንዲሰጥ አሳማኝ የሚያደርግ በመሆኑ (በደምቦቹ ላይ በተቀመጡት ሁኔታዎች መሰረት የጥገኛው ልጅ ጥቅሞች ተመራጭ የሆነውን ጭምር)፣
    d. ምርመራዎች ፍቃድ ባላቸው የማህበራዊ ሰራተኞች መደረግ አለባቸው። ሌላ ምክንያታዊ የጤና እና የደህንነት ውሳኔዎች ለመስጠት በመምሪያው አስፈላጊ መሆናቸውን የታመነባቸው የሰለጠኑ ባለሞያዎች እንደ ሀኪሞች፣ነርሶች ወይም ሳይኮሎጂስቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።
    e. ወጣት ነፍሰጡር ወይም እናት እና የአመልካች ወይም የተቀባይ ጥገኛ ልጅ ከወጣት ነፍሰጡር ወይም እናት ወላጅ፣ ህጋዊ ሞግዚት፣ ወይም ሌላ አዋቂ ዘመድ ወይም በዚህ ክፍል ንኡስ ክፍል (e)(1) ውስጥ በተገለጸው ስፍራ እንዲኖሩ ሲገደዱ፣ TANF እንደ መጠበቂያ ክፍያ መልኩ ሊከፈል ይችላል።
        i. ወጣት ነፍሰጡር ወይም እናት ቤት የመኖር መስፈርት ቀሪ ከተደረገ፣ መምሪያው ለወጣት ነፍሰጡርዋ ወይም እናት የሁለተኛ እድል ቤት፣ የወላጅነት ቤት፣ ወይም ሌላ ተገቢ የሆነ በአዋቂ ክትትል የሚደረግበት ደጋፊ የአኗኗር ሁኔታን ማቅረብ ወይም መደገፍ አለበት፣ መምሪያው የወጣት ነፍሰጡር ወይም እናት ያሁኑ የአኗኗር ሁኔታ ተገቢ ነው ብሎ ካልወሰነ በስተቀር። መምሪያው ለወጣት ነፍሰጡር ወይም እናት የመኖሪያ ስፍራ በማቅረብ ወይም በማፈላለግ ድጋፍ ሲያደርግ የወጣት ነፍሰጡርዋን ወይም እናት እና ልጅ ፍላጎቶች እና ስጋቶች ታሳቢ ማድረግ አለበት። መምሪያው ከዚያ በኋላ ለወጣት ነፍሰጡር ወይም እናት ተገቢ የሆነውን የአኗኗር ሁኔታ ይወስናል እና ቀጣይነት ያለው የTANF ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ወጣት ነፍሰጡርዋ ወይም እናት እና ጥገኛው ልጅ በዚያ የአኗኗር ሁኔታ እንዲኖሩ ይጠይቃል። መምሪያው የወጣት ነፍሰጡርዋ ወይም ሁኔታዎች መቀየራቸውን ከወሰነ እና የአሁኑ አኗኗር ተገቢነቱ ከቀረ፣ ወጣቷ ነፍሰጡር ወይም እናት በአማራጭ ተገቢ አኗኗር ልትኖር እና የTANF ጥቅማጥሞችን መቀበልዋን መቀጠል ትችላለች።

***የTANF እና POWER የበቂ ምክንያት ማረጋገጫ***

የመጀመሪያ ገለጻ፣ ምክር፣ ወይም የምዘና ተግባራት ላይ አለመገኘት፣ ወይም ሌላ የስራ ዝግጁነት ወይም የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴ ላይ ለመሳተፍ ወይም ለማጠናቀቅ አለመቻል ወይም በESA እንደተገለጸው በስራ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ አለመቻል፣ ከሚከተሉት ውስጥ አንድ (1) ወይም ከዚያ የበለጠ ያካትታል

a) የተረጋገጠ፣ አስፈላጊ ከሆነ፣ የአመልካቹ ወይም የአመልካቹ ቤተሰብ አባል ወይም የቅርብ ዘመድ የአካል ወይም የአእምሮ ህመም ወይም የህክምና ሁኔታ ወይም ማንም ተገቢ የሆነ የቤተሰብ አባል ወይም ቤተሰብ አስፈላጊውን የህክምና እንክብካቤ ለመስጠት ያልተገኘ እንደሆነ፣ ይህም አመልካቹ ወይም ተቀባዩ በሚፈለጉት ተግባሮች እንዳይሳተፍ የከለከለው እንደሆነ።

b) ተገቢ እና ተመጣጣኝ የሆነ የልጅ እንክብካቤ (መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ) ከአመልካች ቤት ወይም የአገልግሎት ስፍራ ምክንያታዊ በሆነ ርቀት ላይ የሌለ ከሆነ፣ አመልካች በእንቅስቃሴዎች ውስጥ ለመሳተፍ ወይም መሳተፍ ለመቀጠል ወይም ቅጥር ለመቀበል የህጻን እንክብካቤ አስፈላጊነት ይኖራል። ለዚህ ምእራፎች አላማ፣ አመልካች በትምህርት ቤት መደበኛ ክትትል እንዳያደርጉ የሚከለክል እድሜው ከስድስት (6) ያነሰ ህጻን ወይም ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ያለውን ህጻን (ብቃት ባለው የህክምና ማስረጃ፣ በ ESA እንደተወሰነው የተረጋገጠ) የሚንከባከቡ ከሆነ፣ የልጅ እንክብካቤ አስፈላጊነት አለ።

c) አመልካች እድሜው ከስድስት (6) በታች የሆነ ህጻን ወላጅ ወይም ሌላ ተንከባካቢ ለልጁ እራሳቸው እንክብካቤ የሚያደርጉ፣ እና በስራ ቅጥር እንቅስቃሴዎች ላይ፣ በአማካኝ ቢያንስ ሀያ (20) ሰዓታት በሳምንት የሚሳተፉ ናቸው፤

d) አመልካች ከፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ በጣም ራቅ ያለ ቦታ የሚኖሩ በመሆኑ ማጓጓዣ አይገኝም። ግለሰቡ ልጆችን ወደ እና ከልጅ እንክብካቤ ማቆያ ወይም ትምህርት ቤት ለማመላለስ ከሚወስደው ጊዜ ውጭ፣ ወደ መደበኛ ስራ ወይም የስልጠና ቀን ለመሄድ ባለው ምክንያታዊ የህዝብ ወይም የግል ማጓጓዣ ለደርሶ መልስ ጉዞ ከሁለት (2) ሰዓታት በላይ የሚፈጅ ከሆነ ሩቅ ኗሪ ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ። ነገር ግን፣ በስፍራው መደበኛ የጉዞ ሰዓት ከሁለት (2) ሰዓታት በላይ ከሆነ፣ የደርሶ መልስ ጊዜው በቂ ምክንያት ተደርጎ አይቆጠርም።

e) የፌደራል ወይም የግዛት ህጉን በመጣስ መንግስታዊ ባልሆነ ተቋም፣ አሰሪ ወይም ሌላ ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ የሚደረግ አድልዎ፤

f) የስራ ተሳትፎ አበል ሳይከፈል መስራት ወይም መሳተፍ፤

g) በ 29 DCMR § 5811 የተዘረዘሩ የስራ ቦታ መጠበቂያ መብቶችን መጣስ፣ እና

h) አመልካች በሚያስፈልጉት እንቅስቃሴዎች እንዳይሳተፍ የሚከለክል፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ የቤት ቃጠሎ፣ ወይም የመኪና አደጋን ጨምሮ ሌሎች ከአመልካቹ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ከተለመደው ውጭ እና ያልታሰበ ሁኔታ።

የአመልካች የበቂ ምክንያት ጥያቄ የክልከላ ውሳኔ በጽሁፍ መሆን እና በፍትሀዊ ችሎት ሂደት ይግባኝ የሚባልበት ይሆናል። ESA የበቂ ምክንያት ምክንያታዊ የሆነ ማረጋገጫን ሊጠይቅ ይችላል።

***የTANF ጥያቄ ለእድሜ አናሳ ልጆች የትምህርት ቤት ምዝገባ እና የእርጉዝ ወይም ወላጅ ወጣቶች ትምህርት ቤት ክትትል ማረጋገጫ***

የTANF ጥቅማጥቅሞችን ለመቀበል እንደ መስፈርት፣ የትምህርት ቤት ምዝገባ ለእያንዳንዱ እድሜው 16፣ 17፣ ወይም 18 አመት የሆነው ጥገኛ ልጅ እና ለሁሉም እድሜያቸው ከ20 በታች ለሆኑ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወይም ተመጣጣኙን በስኬት ያላጠናቀቁ ወጣት ነፍሰጡር ወይም ወላጅ (ወንድ ወይም ሴት) የትምህርት ቤት ክትትል ማረጋገጫ በቅድመ ሁኔታ ያስፈልጋል። የጥገኛ ልጅ የትምህርት ቤት ምዝገባ ካልተረጋገጠ፣ ልጁ ለእርዳታ ብቁ እንዳልሆነ ይቆጠራል፣ እና ልጁ እድሜው 16፣ 17፣ ወይም 18 ከመሙላቱ በፊት ባለው ወር የመጨረሻ ቀን ከእርዳታ ይሰረዛል። የትምህርት ቤት መገኘት ለነፍሰጡር ወጣት ወይም ወላጅ ካልተረጋገጠ፣ የትምህርት ቤት መገኛ መስፈርቶቹን ላላሟሉበት ለእያንዳንዱ ወር ወጣቱ የTANF ብቃቱን ያጣል።

የምዝገባ ወይም የትምህርት ቤት መገኛ የመቆጣጠሪያ ማረጋገጫ፣ ከታች ከተዘረዘሩት ሰነዶች ውስጥ አንዱን በ45-ቀን የማመልከቻ ሂደት ክፍለ ጊዜ ወይም ተገቢ በሆነው የዳግም ማረጋገጫ ወይም ለውጥ ሪፖርት የማድረጊያ ቀን ለአገልግሎት ማእከል ማቅረብ ይችላሉ።

- የትምህርት ቤት መገኛ የመቆጣጠሪያ ቅጽ፣
- ላሁኑ የትምህርት አመት በጣም በቅርብ ጊዜ የተሰጠ ሪፖርት ካርድ፣
- ከትምህርት ቤት ሃላፊዎች ጋር የተደረጉ መጻጻፎች፣
- ከስኮላርሺፕ ቦርዶች ወይም ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር የተደረገ መጻጻፎች፣ ወይም
- በትምህርት ቤቶች የውሂብ መጋራት ስምምነቶች እና ልውውጦች መሰረት ከትምህርት ቤት መዝገቦች የተገኙ መረጃዎች።

የበቂ ምክንያት መስፈርቶች ካልተሟሉ በስተቀር፣ ወጣት ነፍሰጡር ወይም ወላጅ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም ተመጣጣኙን የትምህርት፣ ስልጠና፣ ወይም ሌላ በመምሪያው ተቀባይነት ያለው ፕሮግራም ላይ መከታተል አለባቸው። የትምህርት ቤት መገኛ የመቆጣጠሪያ መስፈርቶችን ላለማክበር በቂ ምክንያቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

- የወጣትዋን መደበኛ ትምህርት ቤት መገኘት የሚከለክል፣ በDHS ዳይሬክተር ወይም የሱ ወይም የሷ ተወካይ በሚወሰነው ብቃት ባለው የህክምና ማስረጃ የሚረጋገጥ የወጣቱ ልጅ ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች አሉት፤
- በDHS የሚወሰን ወጣቱን በሚፈለገው እንቅስቃሴዎች እንዳይሳተፍ የሚከለክል ከወጣቱ/ጧ ቁጥጥር ውጪ የሆነ መደበኛ ያልሆነ እና ያልታሰበ ሁኔታ።
- ከ12 ሳምንታት ያነሰ እድሜ ልጅ ያለው/ያላት
- ከትምህርት ቤት በበቂ ርቀት ተገቢ የሆነ የልጅ እንክብካቤ አለመገኘት፣ ዋጋው ተመጣጣኝ አለመሆን፣ ወይም ተስማሚ ያልሆነ እና እንክብካቤ የሚያስፈልገው ልጅ ከስድስት አመት ያነሰ ነው፣
- መቅረቱ በትምህርታዊ ወይም የስልጠና ተቋም ወይም ፕሮግራም "ይቅርታ የሚያሰጥ" ሆኖ የሚቆጠር

***የTANF መታለፎች***

እንደ TANF ተሳታፊ፣ ከሥራ ተግባራት፣ የግለሰብ ሀላፊነት እቅድን ማጠናቀቅ፣ የሥራ ፍለጋ፣ እና የሥራ ዝግጁነት ተግባራትን ጨምሮ፣ ለመታለፍ የመጠየቅ መብት አለዎት፣ የሚከተሉት ከሆኑ፦

- በእድሜ አናሳ የቤተሰብ መሪ ያልሆነ ከሆኑ፣ የተከፋይ-ብቻ ጉዳዮች ላይ ያሉ በእድሜ አናሳ የሆኑትን ጨምሮ፤
- ከአስራ ሁለት (12) ወራት እድሜ በታች የሆነ/ች ልጅ ያላቸው ላጤ አሳዳጊ ወላጅ ወይም የእንክብካቤ ሰጪ፣ ማንም ወላጅ ለእንደዚህ ያለ መታለፍ ለአስራ ሁለት (12) ወራት በላይ ብቁ ሊሆኑ እስከማይችሉ ድረስ፤

- ከስድስት (6) ዓመት እድሜ በታች ለሆነ/ች ልጅ በግል እንክብካቤ እየሰጡ ያሉ ላጤ የሆኑ አሳዳጊ ወላጅ ወይም የእንክብካቤ ሰጪ፣ ወላጅ ወይም እንክብካቤ ሰጪ፣ በDHS እንደተወሰነው፣ አስፈላጊውን የልጅ እንክብካቤ ለማግኘት አለመቻላቸውን ካሳዩ፣ ምክንያቱም፥
  - ተገቢ እና ተመጣጣኝ መደበኛ የልጅ እንክብካቤ አይገኝም፤
  - ኢ-መደበኛ የልጅ እንክብካቤ (እንደ በዘመድ የሚደረግ ዓይነት) አይገኝም ወይም ምቹ አይደለም፤ ወይም
  - ተገቢ የልጅ እንክብካቤ፣ መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ የሆነ፣ ከወላጅ ወይም ተንከባካቢ ቤት ወይም የሥራ ፍለጋ/የሥራ ዝግጁነት ቦታ አግባብ የሆነ ርቀት ላይ አይገኝም፤
- ተቀዳሚ ደሞዝ አምጪ ያልሆነ እና ከስድስት (6) ዓመት በታች እድሜ ላለው/ላላት ልጅ በግል እንክብካቤ የሚሰጡ፣ የሁለት-ወላጅ ወይም ሁለት-ተንከባካቢ እርዳታ ክፍል ውስጥ ወላጅ ወይም ተንከባካቢ የሆኑ (በተቀዳሚ ደሞዝ አምጪ ስራ አጥነት ምክንያት የእርዳታ ክፍሉ ለTANF ብቁ ከሆነ)፣ በDHS እንደተወሰነው፣ አስፈላጊውን የልጅ እንክብካቤ ለማግኘት አለመቻላቸውን ካሳዩ፣ ምክንያቱም፥
  - ተገቢ እና ተመጣጣኝ መደበኛ የልጅ እንክብካቤ አይገኝም፤
  - ኢ-መደበኛ የልጅ እንክብካቤ (እንደ በዘመድ የሚደረግ ዓይነት) አይገኝም ወይም ምቹ አይደለም፤ ወይም
  - ተገቢ የልጅ እንክብካቤ፣ መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ የሆነ፣ ከወላጅ ወይም ተንከባካቢ ቤት ወይም የሥራ ፍለጋ/የሥራ ዝግጁነት ቦታ አግባብ የሆነ ርቀት ላይ አይገኝም፤
- የሁለት-ወላጅ ወይም ሁለት-ተንከባካቢ እርዳታ ክፍል ውስጥ ሁለቱም ወላጆች ወይም ተንከባካቢዎች የሆኑ (በአንድ ወላጅ ወይም ተንከባካቢ አቅም ማጣት ምክንያት የእርዳታ ክፍሉ ለTANF ብቁ ከሆነ)፣ አቅም-ያላጣ ወላጅ ወይም ተንከባካቢ ከስድስት (6) ዓመት በታች እድሜ ላለው/ላላት ልጅ በግል እንክብካቤ የሚሰጡ ከሆነ፣ እና በዳይሬክተሩ እንደተወሰነው፣ አስፈላጊውን የልጅ እንክብካቤ ለማግኘት አለመቻላቸውን ካሳዩ፣ ምክንያቱም፥
  - ተገቢ እና ተመጣጣኝ መደበኛ የልጅ እንክብካቤ አይገኝም፤
  - ኢ-መደበኛ የልጅ እንክብካቤ (እንደ በዘመድ የሚደረግ ዓይነት) አይገኝም ወይም ምቹ አይደለም፤ ወይም
  - ተገቢ የልጅ እንክብካቤ፣ መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ የሆነ፣ ከወላጅ ወይም ተንከባካቢ ቤት ወይም የሥራ ፍለጋ/የሥራ ዝግጁነት ቦታ አግባብ የሆነ ርቀት ላይ አይገኝም፤
- ታማሚ የሆነ ሰው፣ ህመሙ ወይም ጉዳቱ የሥራ ተግባራት ውስጥ ተሳትፎን እንደሚከለክል በተወዳዳሪ የህክምና ማስረጃ (ወይም ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው መሰረቶች) መሰረት DHS ከወሰነ።
- አቅም-ያጣ የሆነ ሰው (ከልጅ መውለድ በኋላ በሀኪም የታዘዘ ማገገሚያ ጊዜን ጨምሮ)፣ በሀኪም ወይም ፈቃድ ባለው ውይም የምስክር ወረቀት ባለው የስነ-ልቦና ባለሙያ የተወሰነው አካላዊ ወይም የአዕምሮ እክል ግለሰቡ የስራ ተግባራት ውስጥ እንዳይሳተፍ እንደሚከልክል DHS ካረጋገጠ፤
- ስልሳ (60) ዓመት ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ያለው ሰው፤
- ሌላ የቤተሰብ አባል በህመም ወይም አቅም-ማጣት ምክንያት (በሀኪም ወይም ፈቃድ ባለው ወይም ምስክር ወረቀት ባለው የስነ-ልቦና ባለሙያ እንደተወሰነው) የግለሰቡን መኖር በመፈለጉ በቤት ውስጥ የሚፈለግ ሰው፣ እና የሚያስፈልገውን እንክብካቤ ለማቅረብ ሌላ ተገቢ የቤተሰብ አባል ከሌለ፤
- እርጉዝ የሆነች ሴት እና በሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ትራይምስተር ውስጥ ስለመሆኗ የህክምና ማረጋገጫ ያቀረበች፤
- በአድን (1) ወላጅ የእርዳታ ክፍል ውስጥ ያለ ሰው ሆኖ፣ የሚከፈልበት ወይም የጸደቀ የበጎ ፈቃድ ስራ ውስጥ የሚሰራ፣ የጸደቀ የስራ ልምድ ያለው፣ ወይም በንዑስ-ክፍል 29 DCMR § 5804.2 እንደተቀመጠው የስራ ተሳትፎ መጠን ለማሟላት ለሚሆን የዝቅተኛ ሰዓታት በዲስትሪክት ህግ ስር እንደ ስራ የሚቆጠር ሌላ ተግባር ውስጥ የሚሳተፍ፤
- በሁለት (2) ወላጅ የእርዳታ ክፍል ውስጥ ያሉ አዎች ሆነው፣ የሚከፈልበት ወይም የጸደቀ የበጎ ፈቃድ ስራ ውስጥ የሚሰራ፣ የጸደቀ የስራ ልምድ ያለው፣ ወይም ቢያንስ ሰላሳ አምስት (35) ሰዓቶች በሳምንት (ወይም በአማካይ በወር አንድ መቶ አርባ (140) ሰዓቶች)፣ በዲስትሪክት ህግ ስር፣ እንደ ስራ የሚቆጠር ሌላ ተግባር ውስጥ የሚሳተፍ፤
- የሙሉ-ጊዜ VISTA (Volunteers In Service to America/ቮሉንቲርስ ኢን ሴርቪስ ቱ አሜሪካ) ወይም Americorps volunteer (አሜሪኮርፕስ ቮሉንቲር)፤ እና
- በዲስትሪክት-የሚደገፍ የTANF ድርሻን በተመለከተ፣ የአካባቢ፣ የጸደቀ የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታዊ ተቋማት ውስጥ የተመዘገቡ ግለሰቦች።

የ TANF አመልካች ወይም ተቀባይ ከ DHS በማንኛውም ጊዜ፣ በቃል ወይም በጽሁፍ፣ መታለፍን መጠየቅ ይችላሉ። የመታለፍ ጥያቄዎች አመልካች ወይም ተቀባይ የተጠየቀውን መታለፍ ለመደገፍ ተገቢ እና አስፈላጊ ማረጋገጫን ካስገቡ በኋላ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናሉ። DHS የመታለፍ ጥያቄውን ውድቅ ካደረገ፣ በጽሁፍ፣ ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት በመግለጽ፣ እና ውድቅ መደረጉን ይግባኝ ለማለት የሚጠቅም ሂደትን በማብራራት ይሆናል።

መታለፍን እንደሚሟሉ DHS ከወሰነ፣ በፈቃድዎ ማንኛውም የስራ ተግባር ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ። የTANF አመልካቾች ወይም ተቀባዮች እንደ SNAP ወይም Medicaid ላሉ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

*ፊርማ*

- እኔ የልጅ ድጋፍ ትብብር እና ላለመተባበር በቂ ምክንያት ማስታወቂያውን መቀበሌን አረጋግጣለሁ።
- እኔ ለTANF ፕሮግራም የቤት መኖር መስፈርቶችን አለማሟላት ማስታወቂያውን መቀበሌን አረጋግጣለሁ።
- እኔ ለTANF ፕሮግራም የበቂ ምክንያት መስፈርቶች ማረጋገጫ ማስታወቂያውን መቀበሌን አረጋግጣለሁ።
- እኔ ለTANF ፕሮግራም አካለመጠን ያልደረሱ ልጆች የትምህርት ቤት ምዝገባ ማረጋገጫ እና የወጣት ነፍሰጡር ወይም ወላጅ ትምህርት ቤት የመገኘት መስፈርቶችን ማስታወቂያውን መቀበሌን አረጋግጣለሁ።

- እኔ ለTANF ፕሮግራሞች የTANF መታለፎች ማስታወቂያ እንደደረሰኝ እውቅና እሰጣለሁ።

እዚህ ይፈርሙ፥ ቀን፥

________________________________________ ________________________

ደንበኛ ወይም ስልጣን ያለው ተወካይ ፊርማ

**TANF (ጊዜያዊ እርዳታ ለችግረኛ ቤተሰቦች)**

እንደ TANF ዳግም-ማረጋገጫዎ ሂደት አካል፣ ገለጻ፣ምዘናን ማጠናቀቅ እና የመጀመሪያ የራስ ማብቃት እቅድ ማዘጋጀት፣ እንደ በሂደት ላይ ያለ የTANF ጥቅማጥቅሞች ብቁነት መስፈርት በዲሲ ይፋዊ ኮድ § 4–205.19a እንደሚገደደው። እርስዎ የተጨማሪ ዋስትና ገቢ (SSI) እያገኙ ከሆነ ወይም የራስዎ ያልሆነ ልጅ ተንከባካቢ እና ዳግም-የሚያረጋግጡት ለልጁ(ጆቹ) ብቻ ከሆነ፣ ይህ መስፈርት ለእርስዎ ተፈጻሚ አይሆንም። ለምዘና ቀጠሮ ለማስያዝ፣ የDHS የስራ እድል ቢሮ(OWO)፣ የቤተሰብ መገልገያ ማእከል ጋር በ (202) 698-1860 ይደውሉ እና የተሞላውን ግምገማ የIRP እውቅና መስጠት ቅጽ ጋር አያይዘው ያምጡ። በተጨማሪ፣ የጥቅማጥቅምዎ መጠን ትክክል እንዳልሆነ ካሰቡ፣ ከዚያ ፍትሀዊ ችሎት ሊያገኙ ይችላሉ።

የማንኛውም አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ከቤት መቅረት፣ መቅረቱ ዘጠና (90) ቀናት በላይ ከሆነ ሪፖርት ማድረግ የእርስዎ ሃላፊነት ነው። አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ያለበቂ ምክንያት በ 29 DCMR §5802.2 ላይ እንደተተረጎመው ከዘጠና (90) ቀናት በላይ የቀረ እንደሆነ ወይም እንዲቀር የሚጠበቅ ከሆነ፣ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የTANF ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ አይሆንም። እርስዎ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ከዘጠና (90) ቀናት በላይ የቀረ መሆኑን ወይም የሚቀር መሆኑን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ቀናት ውስጥ ሪፖርት ካላደረጉ፣ በቂ እና በሰአቱ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለሶስት (3) ወራት ያክል የወላጅ ወይም ተንከባካቢ ዘመድ ፍላጎቶች ከTANF ጥቅማጥቅሞች ውጪ ይሆናሉ። የአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ከዘጠና (90) ቀናት በላይ መቅረት፣ ወይም የሚቀር መሆኑን ዘግይተው ሪፖርት ካደረጉ፣ ለአንድ (1) ወር ያክል፣ ልጁ ከቤት ከቀረበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ የወላጅ ወይም ተንከባካቢ ዘመድ ፍላጎቶች ከTANF ጥቅማጥቅሞች ውጪ ይሆናሉ።

**<u>POWER(የስራ ቅጥር እና ሃላፊነት ፕሮግራም)፣</u>** ለTANF ጥቅማጥቅሞች ብቁ ከሆኑ እና መስራት የማይችሉ ከሆነ በማንኛውም ጊዜ በጊዚያዊነት ወደ POWER ለመዘዋወር ማመልከት ይችላሉ። እርስዎ መስራት የሚከለክልዎ የአካል ወይም የአእምሮ ሁኔታ መኖሩን ለኛ በማሳወቅ ለPOWER ማመልከት ይችላሉ። በተጨማሪ እርስ ለPOWER ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ እርስዎ ከሆኑ፣

- ከ19 አመት በታች ወጣት ነፍሰጡር ወይም እናት እና በትምህርት ቤት የተመዘገቡ
- በቤትዎ ውስጥ ያለ የአካል ወይም የአእምሮ ችሎታ ያጣ ሰውን መንከባከብ የሚኖርብዎ ከሆነ
- እርስዎ 60 አመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ
- እርስዎ የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባ ከሆኑ።

<u>በTANF ውስጥ ሆነው መሳተፍዎ ዋጋ አለው፣</u> ከTANF አቅራቢዎችዎ ጋር ሲሳተፉ፣ ለአበሎች እና ጉርሻ(ዎች) ብቁ ኖት። ይህ ለእርስዎ እና የእርስዎ ቤተሰብ ተጨማሪ ገንዘብ ያስገኛል።

<u>ቅጣቶች፣</u> እርስዎ እቅድዎን ወይም የስራ መስፈርቶችዎን ካላከበሩ፣ የTANF ጥቅማጥቅሞችዎ በቂ ምክንያት ከሌሎት በስተቀር ይቀነሳል። ይህ የስራ ቅጣት ተብሎ ይጠራል። እኛ ለራስዎ እና ለልጆችዎ ስኬታማ እንዲሆኑ እራስዎን በተገቢው ቦታ እንዲያስቀምጡ እንፈልጋለን። DHS ለስራ ለመዘጋጀት እና ለማግኘት እርስዎን ለመርዳት አገልግሎቶችን ያቀርባል፣በስራ ላይ ስኬታማ እንዳይሆኑ የሚከለክልዎትን ችግሮች ይመለከታል፣ እና የተሻለ ስራ እንዲያገኙ ይረዳል። እርስዎ ሊቀጡ ከሆነ፣ ቀድም ብሎ እንዲያውቁት እናደርጋለን።

<u>EBT(የኤሌክትሮኒክ የጥቅማጥቅም ዝውውር)፣</u> የEBT ካርድ የእርስዎን ጥቅማጥቅሞች ለማግኘት የሚጠቀሙበት ካርድ ነው። እርስዎ የEBT ካርድዎን በመጠጥ መደብሮች፣ ቁማርቤቶች(ካዚኖዎች)፣ ወይም የራቁት ዳንስ ክለቦች እንዲጠቀሙ አይፈቀድሎትም። ካርዱን በእነዚህ ስፍራዎች በማናቸውም ከተጠቀሙ፣ ግብይቱ ይታገዳል። DHS በእነዚህ ስፍራዎች የካርዱን አጠቃቀም ይቆጣጠራል። የTANF ጥቅማጥቅሞችዎን በEBT ካርድዎ በእነዚህ በተከለከሉ ቦታዎች መጠቀምዎን ለDHS ሪፖርት አለማድረግ በDC ይፋዊ ህግ §4-218.01(c) ላይ የህዝብ እርዳታ ማጭበርበር አንቀጾችን በመጣስ የመሸሽግ ተግባር እንደሆነ ይቆጠራል። [(http://www.lexisnexis.com/hottopics/dccode/)።](http://www.lexisnexis.com/hottopics/dccode/) ከላይ

ባለው ኮድ መሰረት ዲስትሪክቱ ቅጣቶችን ሊጥል ይችላል። እርስዎ ካርዱን በተከለከሉ ቦታዎች ላይ ከተጠቀሙ ፍላጎቶችዎ ከቤተሰብዎ TANF ጥቅማጥቅም ሊወገድ እና ከፕሮግራሙ ለዘለቄታው ሊሰረዙ ይችላሉ።

<u>የቤት ውስጥ ጥቃት፣</u> በማናቸውም ጊዜ ከTANF የስራ መስፈርቶች እና የTANF የልጅ ድጋፍ ትብብር መስፈርቶች ቀሪ እንዲደረጉ፣ እርስዎ የቤት ውስጥ ጥቃት በቂ ምክንያት የመጠየቅ መብት አሎት። DHS የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎችን

አግባብ ላላቸው አገልግሎቶች ሪፈር ያደርጋቸዋል። የቤት ውስጥ ጥቃት መግለጽ በፍቃደኝነት ነው እና እርዳታ የመቀበል ችሎታን በከፍተኛ ሁኔታ አይጎዳም ወይም አያዘገይም። የተገለጸ መረጃ ሚስጥራዊ ነው፤ ነገር ግን፣ ስለ ህጻን ጥቃት፣ ህጻን ቸል ማለት ወይም የአረጋውያን መበዝበዝ ለልጅ ጥበቃ አገልግሎቶች ወይም ለዲስትሪክቱ የእርጅና እና ማህበረሰብ ኑሮ (DACL) የአዋቂ ጥበቃ አገልግሎቶች ክፍል (APS) ሪፖርት መደረግ አለበት።

**የPOWER ብቃት**

የድጋፍ ክፍል በሚከተሉት ሁኔታዎች ለPOWER ብቁ ይሆናል፣

- የድጋፍ ክፍሉ ራስ የአካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ ነው፣

- የድጋፍ ክፍሉ ራስ አካላዊ ወይም አእምሯዊ ችሎታ አጥቷል፣ እና
- የድጋፍ ክፍሉ ራስ የአካል ወይም የአእምሮ ችሎታ ማጣት ብቃት ባለው የህክምና ማስረጃ ተረጋግጧል እና ከድጋፍ ክፍሉ ራስ እድሜ፣ የቀድሞ የስራ ልምድ፣ ትምህርት፣ እና በድጋፍ ክፍሉ ራስ የመስራት ችሎታ ላይ አስተዋጽኦ ያላቸው፣ በESA ተገቢ እንደሆኑ በተወሰኑ ነገሮች።
    - የድጋፍ ክፍሉን ራስ የመስራት ወይም የስራ ፍለጋ ላይ መሳተፍ ወይም የስራ ዝግጁነት እንቅስቃሴዎች ላይ በጉልህ መልኩ ካገደ፣ እና
    - ከ30 ቀናት በላይ ሊፈጅ እንደሚችል ከታሰበ።

ከላይ ካሉት ሁኔታዎች በተጨማሪ፣ የድጋፍ ክፍሉ ራስ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አባት ከሆነ፣ የድጋፍ ክፍሉ ለPOWER ብቃት ሊኖረው ይችላል፣

- በህክምና አስገዳጅነት ምክንያት፣ የአካል ወይም የአእምሮ ችሎታ ያጣን የቤተሰብ አባል ለመንከባከብ ቤት ውስጥ ይፈለጋል፣ ወይም
- በመምሪያው የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባ መሆናቸውን የተወሰነ እና አስፈላጊ የሆነ የድጋፍ ምክር እና አገልግሎቶችን እያገኙ ያሉ እና የቤት ውስጥ ጥቃት ምዘና በመምሪያው ተወካይ ያደረገ እና ይህም የስራ መስፈርት ወይም የልጅ ድጋፍ ትብብር ቀሪ እንዲሆን ምክራዊ አስተያየትን ያስገኘበት፣ ወይም
- ወጣት ነፍሰጡር ወይም ወላጅ እሷም፣
    - በመምሪያው ከቤት መኖር መስፈርቶች ቀሪ እንድትሆን ማረጋገጫ የተሰጠበት፣
    - በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የአጠቃላይ ትምህርት ተመጣጣኝ ዲግሪ ፕሮግራም ላይ ከተመዘገቡ፣ እና፣
- ከእሷ ወይም የሱ TANF የግለሰብ ሃላፊነት እቅድ (IRP) ወይም በPOWER ተሳትፎው/ዋ ወቅት የተሰራ ማንኛውም ተመጣጣኝ እቅድን በሚጣጣም መልኩ የሷን ወይም የሱን የስራ መስፈርቶች ያሟላል።

ግለሰቡ ለPOWER ብቁ አይሆንም ያ ግለሰብ ከተቀበለ

- Temporary Assistance for Needy Families (TANF) (ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ)፤
- ተጨማሪ የዋስትና ገቢ፤ ወይም
- የስራ አጥ የካሳ ጥቅማጥቅሞች።

**የልጅ ድጋፍ መብቶች (TANF)**

ሁሉም የልጅ ድጋፍ ክፍያዎች በCSSD በኩል ይሰበሰቡ እና ይሰራጫሉ። እርስዎ የድጋፍ መብቶችዎን እስከ TANF የገንዘብ ድጋፍ መጠን ድረስ እየወከሉ ነው እና እርስዎ ካሁኑ የወርሀዊው የልጅ ድጋፍ ግዴታ ላይ የመጀመሪያውን $150.00 ሊያገኙ ይችላሉ ወይም ከማይረዳ ወላጅ ወይም የትዳር አጋር በፈቃድ የተደረገ የልጅ ድጋፍ ክፍያ እና ማንኛውም ከTANF የገንዘብ ድጋፍ በላይ። እርስዎ በስህተት ክፍያ ከተቀበሉ እባክዎ በአፋጣኝ CSSDን ያግኙ። እርስዎ በስህተት ክፍያ ከተቀበሉ እና ክፍያውን ካልመለሱ፣ CSSDን መልሰው እንዲከፍሉት ሊገደዱ ይችላሉ። በእነዚህ ሁኔታዎች ካልተስማሙ፣ TANF ማግኘት አይችሉም። እርስዎ ከTANF አንድ ጊዜ ከወጡ፣ እርስዎ ማንኛውንም ያለ የልጅ ድጋፍ ክፍያዎቹን እንደወሰዱ ይቀራሉ። እርስዎ የTANF ጥቅማጥቅምን የሚጠቀሙ ከሆነ፣ እርስዎ በእነዚህ ሁኔታዎች የሚስማሙ መሆኑን ለኛ እየነገሩን ነው።

## SNAP ብቻ

**የማህበራዊ ደህንነት ቁጥር መግለጫ፥**

በፌዴራል ሕግ ስር፣ SNAP ቤተሰብ ዉስጥ ካሉ የማህበራዊ ደህንነት ቁጥርዎን (SSN) (ካለዎት) ማቅረብ ይኖርቦታል። (*የ2008 የምግብ እና አመጋገብ ተግባር ይመልከቱ*, እንደተሻሻለ, 7 U.S.C. § 2025(e) እና *የማህበራዊ ደህንነት ቁጥሮች*, 7 CFR § 273.6) የማይሳተፉ ቤተሰቦች ወይም የቤተሰብ አባላት ስለዜግነት ወይም የስደተኝነት ሁኔታ፣ SSNs ወይም መረጃ ማቅረብ አይኖርባቸዉም። የእርስዎ SSN ማንነትዎን ለማረጋገጥ፣ እጥፍ ጥቅማጥቅሞችን ከመቀበል ለመከላከል፣ እና የሚያስፈልጉትን የፕሮግራም ለውጦች ለማድረግ አገልግሎት ላይ ይውላሉ። የDHS የኮምፒውተር ሲስተም የእርስዎን ገቢ ለማረጋገጥ ከፌደራል እና ከአካባቢ ምንጮች፣ የአገር ውስጥ ገቢ አገልግሎት፣ ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የDC የስራ ቅጥር አገልግሎቶች ዲፓርትመንት፣ እና የDC የልጅ ድጋፍ አገልግሎት ክፍልን (CSSD)። ያለ በቂ ምክንያት SSN ለማቅረብ ፍቃደኛ አለመሆን ወይም ያለመሳካት፣ SSN የማይገኝለት ግለሰብ ዉድቅ መደረግን ያስከትላል።

**የማጭበርበር ቅጣቶች፣** የSNAP ማጭበርበር፣ የSNAP ጥቅማጥቅሞችን ካሸጡ፣ ወይም ሌሎች የSNAP ፕሮግራም ደንቦችን መስበርን ከፈፀሙ፣ እንግዲህ ተቀጥተዉ እስከ 20 ዓመታት ሊታሰሩ ይችላሉ። የሰበሯቸው ደንቦች ላይ በመመስረት፣ ከአንድ ዓመት የትም ቦታ እስከ ዘላቂነት ጥቅማጥቅሞችዎን ሊያጡ (ዉድቅ ሊደረጉ) ይችሉ ይሆናል። የዉድቅ መደረጊያ ቅጣቶች 7 C.F.R. § 273.16(b) እና 7 U.S.C. § 2015(b) ዉስጥ ተዘርዝሯል።

## SNAP እና ጥሬ ገንዘብ

- ይህ ቅጽ ከዘገየ ወይም ያልተሟላ ከሆነ፣ የእርስዎን ጥቅማጥቅሞች በጊዜ ላያገኙ ይችላሉ።
- ይህንን ቅጽ የማይመልሱ ከሆነ፣ የእርስዎን ጉዳይ እንዘጋለን።
- በዚህ ቅጽ ዉስጥ የጠየቅነዉን ማስረጃ በጊዜ የማይመልሱ ከሆነ፣ የእርስዎን ጉዳይ ሊንዘጋ እንችላለን ወይም ሊበቁለት ከሚችሉት በታች ያነሰ ጥቅማጥቅሞችን ሊያገኙ ይችላሉ።
- የርስዎ ጉዳይ ከተዘጋ፣ ሌላ ማመልከቻ እንዲሞሉ ሊያስፈልጎት ይችላል።
- የርስዎን ጥቅማጥቅሞች ለመቀነስ ወይም ለማቆም የተላለፈ ዉሳኔ ላይ የማይስማሙ ከሆነ፣ የፍታዊ መስማያ መብት አለዎት። ስለጥቅማጥቅሞችዎ የትኛዉንም መቀነስ ወይም ማቆም፣ ማሳወቂያ ይላክሎታል።

This page intentionally left blank

## TANF ብቻ

### ግምገማ እና የIRP እውቅና መስጫ ቅጽ

ይህንን ገጽ ያንብቡ፣ ይፈርሙ፣ እና ወደ ቀጠሮዎ ይዘውት ይምጡ – ከታች ይመልከቱ)

ለTANF (ጥሬ ገንዘብ) ጥቅማጥቅሞች ተቀባይነት ለማግኘት፣ ምክራዊ ገለጻ/ምዘና ማጠናቀቅ እና የግለሰብ የሃላፊነት እቅድ (IRP) መፈረም አለብዎት። ይህ መጠናቀቅ ያለበት ለጥቅማጥቅሞች ይህን ዳግም-ማረጋገጫ ካስገቡ ጀምሮ በ45 ቀናት ውስጥ ነው።

**ቀጠሮ እንዴት ነው የማስይዘው?**

ቀጠሮ ለማስያዝ በ**(202) 698-1860** መደወል ወይም የቤተሰብ የስራ እድል ቢሮ በሚገኝበት ባንዱ ስፍራ መምጣት አለብዎት። ቀጠሮዎች የሚሰጡት ከሰኞ-ሐሙስ ከጥዋቱ 8:15-3:00 ነው።

| | |
|---|---|
| **Anacostia**<br>2100 Marthin Luther King Jr. Ave. S.E Suite 300<br>Washington, D.C. (ዋሺንግተን፣ ዲሲ) 20020 | **Congress Heights**<br>4049 South Capitol Street. SW<br>Washington, DC 20032 |

**የኔ ገለጻ/ምዘና ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል?**

ግምገማው ላይ ቢያንስ 90 ደቂቃዎች ለማሳለፍ እቅድ ይያዙ። ይህን ቀጠሮ መያዝ እና መገኘት የእርስዎ ሃላፊነት ነው።

**ወደ ገለጻየ/ምዘናየ ምን ይዤ መምጣት አለብኝ?**

ይህን ገጽ እና ፎቶ ያለው መታወቂያ ካርድን ማምጣት አለብዎት።

**ወደ/ከ ገለታየ/ምዘናየ ቀጠሮየ ማጓጓዣ ይሸፈናል ?**

ጥያቄ ሲቀርብ በስራ እድል ቢሮ የሜትሮ ድጋፍ/ዋጋ መመለስ ሊደረግ ይችላል።

| የእርስዎ ሙሉ ስም፥ | የትውልድ ቀን፣ | የጉዳይ ቁጥር (የሚታወቅ ከሆነ)፥ |
|---|---|---|
| | | |

እኔ ይህን ገለጻ፣ ምዘና ማጠናቀቅ እና IRP መፈረም አለመቻል የጥቅማጥቅሞች ክልከላ ሊያስከትል እንደሚችል እረዳለሁ።

እዚህ ይፈርሙ፥ ቀን፥

______________________________ ____________________

ደንበኛ ወይም ስልጣን ያለው ተወካይ ፊርማ

የOWO ሰራተኛ ፊርማ፥______________________________የአገልግሎት ማእከል፥____________________ ቀን፥ ________